# የተቃውሞ ሰልፎቻችንን በሚመለከት

(ዳዊት ዳባ)

ዲሲ ላይ ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ነው። በፅሁፍ ለአሜሪካ መንግስት የምናስገባው አቤቱታ የዘት በአፅኖት ሊታሰብበት ይገባል። ግልፅና ጠጣር ባለ መንገድ ቅሬታችን መያዝ አለበት። እስካሁን ጥፋት ሰርተውብናል። አሁንም ቢሆን ሊወስዱ የሚገባቸውን ማስተካከያ እርምጃዎችና ፍላጎታችንን አንድ ሁለት ብሎ ግልፅ ባለ መንገድ የያዘ መሆን አለበት። የአሜሪካን ዜግነት ያለን ስላለንና አቤቱታችን ፍፁም እውነት ስለሆነም እንደ ባለመብት ነው መጠየቅ ያለበት። ከኛ የተሻለ የሚያውቁትን ያገራችንን ተጨባጭ እውነታ መዘርዘሩ በጭራሽ አስፈላጊ አይደለም። በምትኩ እዚህ አገር ከሚኖሩ የብዙ አገር ህዝቦች በተለየና መታከት በሌለበት ተስፋ አድርገንባችሁ ተመሳሳይ ለሆነ ጥያቄና ችግር አሁን ለአንድ ሺ አንድ ጌዜ መሰለፋችን ነው። ይህ እንደሰው ልጅና እንደዜጋ በእኩል ባለመታየታችን በአግባቡ ትኩረት ያልተሰጠን መሆኑን ማሳያ እንደሆነና በዚህ መንገድ እንደምንረዳውም ማስረገጥ ያስፈልጋል። ሰላም አስከባሪ፣ ሽብርተኛን መታገል በሚል የሚቀርበው ሰበብ በአለም ላይ አንደኛ ደሀ በመሆናችንና ረሀብተኛ ህዝብ ላይ የምትወስዱት አድቫንቴጅ መስኳል ሊባሉ ይገባል። ድግሞም ነው። ወንጀል ያልሆነው ወደህግ ስላልወሰድነው ብቻ ነው። ሽብርተኛን በመዋጋት ሰብብ አሸባሪ ሊረዱብንና ዘጠነ ሚሊዮን ያንድ አገር ህዝብ በሽብር ውስጥ ሊኖር ህጋዊነት የለውም። ይህ እኛንም ጨምሮ በየትኛውም አሜሪካዊ ዜጋ ዘንድ አምላካዊ አይደለም። ተቀባይነትም የለውም።

ጥያቄችን መሆን ያለበት የሚመስለኝ (ትልቅ መሆን አለበት)።

- የኢትዬጵያ መሪ ተብዬዎች እስካሁኑ ሰዓት ንፅሀን ዜጎችን የጨፈጨፉ ያለአግባብ ወደ እስር እያጋዙና እያሰቃዩ ያሉ ስለሆነ በአስቸኳይ የጉዞና ማንኛውም በውጪ አገር ያለ ሀብታቸው እገዳ አሁኑኑ እንዲጣልባቸው እንፈልጋለን።

- መንግስት ኢትዮጵያን በሚመለከት የሚከተለው ፖሊሲ ዘጠና ሚሊዮን ህዝብ በሽብር ውስጥ እንዲኖር ነው ያደረገው። ከጠቅላላው ህዝብ ሶስት አራተኛው ዛሬም እርሀብተኛ ነው። እውነታው ኢትዮጵያን በሚመለከት የቀረፃችሁት ፖሊሲ አልሰራም። በሚሰራና አሜሪካን የኢትዮጵያ ህዝብን በዘላቂነት ሊጠቅም በሚችል ፖሊሲ አሁኑኑ ይቀየርልን።

- አሁን በኢትዬጵያ ውስጥ እየተወሰደ ያለውን ፍጅት ለማስቆም መንግስት እየወሰደ ያለው እርምጃ በቂ አይደለም። ጭፍጨፋውን ሊያስቆም አልቻለም። በቀጣይ ሊወሰድ የታሰበ እርምጃ ካለ ማወቅ እንፈልጋለን። ከሌለ ለምን?

- ይህንን አስቀያሚ ዘግናኝ የኢትዬጵያ ሁኔታ ለመለወጥ እየታገሉ ያሉትን ክፍሎች ለመርዳት ያደረጋችሁትን የእስካሁን ስራና እገዛ ካለ ማወቅ እንፈልጋለን። ከሌለ ለምን?።

- ባመት ሶስት ቢሊዬን ዶካር ከአገሪቷ በሚወጣበት ህጋዊ ያልሆነ የጥቅም ጉዳይ አለበት ብለን ስለምንጠረጥር ከአገዛዝ ጋር የተለየ ቅርበትና አፍቃሪ የሆኑ የአሜሪካ መንግስት ባለስላጣናት፣ አማካሪዎች፣ የህዝብ ተወካዬችንም በጨመረ ምርመራ ይደረግልን?። (ይህ ምን አልባት አስፈላጊ ላይሆን ይችላል)

ብቻ ከዚህ በኋላ መሰለፍ ያለብን ለምንጠይቀው የመብትና ህጋዊ ጥያቄ መልስ አላገኘንም ወይ በቂ አይደለም በሚል እንጂ ወያኔ ወንጀል በሰራ ቁጥር አቤቱታ ለማቅረብ ብቻ መሆን

የለበትም። ባለጉዳዬቹ እኛ ነን ደብዳቤ አስገብቶ መመለስ ሳይሆን ተመላልሶ ለጥያቄዎቻችን አጥጋቢ መልስ እንዲሰጡ ማድረጉ የኛ ሀላፊነት ነው። ይህ ሰልፍን ያዘጋጁ ክፍሎች የስራ ድርሻ ነው። ቀጥተኛ የግንኙነት መስመር በሰልፉ እለቱ ማግኘት የግድ አለባቸው። ለጥያቄዎቻችን መልስ መስጠት ደግሞ ግዴታቸው ነው። መልስ ካልሰጡ ወይ መልሱ ካላጠገበን እንደገና መሰለፍም የተቃውሞ መንገዳችን መቀየረም ማሳደግም አብሮ ሊታሰብበት ይገባል።

ሰለማይደመር ነው እንጂ ወያኔ ስልጣን ከተቆናጠጠ ቀን ጀምሮ የገደለው ደርግ ገደለ ከሚባለው በእርግጠኛነት በብዛቱ በልጧል። እንደሰማሁት በኛ ቀበሌ በቀይሽብር የሞቱት ሁለት ዜጎች ናቸው። ወያኔ አዲስ አበባ የገባ ቀን አንድ ብሎ ሶስት ወጣቶችን ቀበሌያችን ውስጥ ገድሏል። ጋንቤላ፣ አፋር፣ ኦጋዴን፣ ደቡብ መቼ ነው በዚህ ደረጃ በማያባራ ሁናቴ ለመቁጠር የሚታክት ፍጅት የነበረው። ብዙ ፍጅት ነበረበት የሚባለውን ጎንደርንም ብንወስድ ወያኔ የገደለው ወይስ ደርግ የገደለው ነው የሚበልጠው?። ያሁኑ እኮ በመላው አገሪቷ ማባርያ የለውም። ለሀያ አምስት አመታት የየቀን ዜና ነው። ቁጥር ውስጥ የገባሁት ለወያኔዎች ሲሆን ፍጅት፣ ርሸና፣ ጭፍጨፋ የሚሉት ቃላትን ብዙዎች ስለማይደፍሩም አግባብም ስለማይመስላቸው ነው። መንግስት ዜጎችን መጨፍጨፍ ይችላል የሚሉ የሰባዊ መብት ተከራካሪዎች እየሰማን ስለሆነም ነው። በእርግጥ እውነታው የማምንበትም አንድም ሆነ አስር ንፁህ ዜጋ ያላግባብ ተገደለ ልዩነት የለውም። በነፃ እርምጃ እሰከተገደሉ በእኩል ሊያናድድንና እስከ ፍርድ ቀን ልንቆጣበት ፍትህን ልንጠይቅበት የሚገባ ነው።

ዛሬ አገሬው ሁሉ በስም በፎቶ በተደገፈ የተጨፈጨፉ ወገኖቹን እያየ፣ በቪዲዬ ጭምር የቀብር ስንሰረዓታቸውን እየተካፈለና አንጀቱ እያረረ ባለበት ገዥዎቻችን በማነለብኝነት በቃ አምስት ነው ብለናል አምስት ነው የገደልነው የሚሉ ናቸው። እኛም ልምድ አድርገነው የተጨፈጨፉ ንፁሀን ዜጎቻችንን ትክክለኛ ቁጥር እያወቅን ውጫዊ አካል ከጠራው ቁጥር ዝንፍ ላለማለት ስንጥር ይታያል። ውጫዊ አካል የምናውቀውን እስኪነግረን ድረስ በፈንጂ ዜጎቻችንን የሚጨርሱት እነሱ እንደነበሩ ልቦናችን አሳምሮ እያወቀው ማንም ግልፅ አድርጎ አይናገረውም ነበር። ሲጋለጥ ፈንጂ መጠቀሙን ጋብ አደረጉ። የተዘነጋ ስለመሰላቸው አሁን ደግሞ በርትተውበታል። ለማንኛውም የዜጎች እሬሳ በየጫካውና ከየጉድባው እየተገኘ ባለበት ሰባት መቶ ብለን በእርግጥ የበኗቸው 599 ቢሆን የሚያስወቅሰን ወይ ውሸታም የምንሆነው እንዴት እንደሆነና ለምኑ መከራ እንደምናይ አይገባኝም።

ትግሬ ገዢዎች የሚፈጁቸውን ወገኖቻችንን የምንቆጥርበት መንገድ አኩኩሉ መሰሏል ነው እያልኩ ያለሁት። ሁሌ በባለተራው ከአንድ ነው የሚጀምረው። በኦሮሚያ በቀጠለው ፍጅት እንኳ ተመሳሳይ ለሆነ ጥያቄ 82 ሰዎች ከአመት በፊት በልተዋቸዋል። ካሁኑ ጋር ሲደመር 286 አካባቢ ደርሷል። በዚህ አቆጣጠር ፍጅቱ አንድ ሳምንት ጋብ ብሎ ቢጀምር አንድ ብለን መቁጠር ልንጀምር ነው ወይ?። ትኩረት አልሰጠነውም እንጂ በዚሁ ሁለት ወራት ውስጥ ብቻ በሌሎቹ ያገሪቷ ክፍሎችም ከሀያ አምስት በላይ ዜጎቻችንን ፈጅተዋል።

አማራውንና ኦሮሞን ለማጣለት ያደረጉት ሙከራ ማክሸፍ መቻሉ እያወቅንበት መሆኑን ያሳያል። በኦሮሚያ የተነሳውን ህዝባዊ አመፁ ለማዳፍን ሲሉ ተሰፋ በቶሎ ይቆርጣሉ ብለን ግን እናዳንዘናጋ። በተጨማሪም በነዚህ ብሔረሰቦች ላይ ባቻ ነው የሚሰሩት ብለን እንዳንሳሳት። ይህው ከወደ ጋንቤላ የምንሰማው ለዚሁ አላማ ሲሉ የሸረቡትን እኩይ ተግባር ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ከበቂ በላይ ምክንያት አላቸው። ቀላል ያደረገላቸውም ምክንያት እንዲሁ። ደቡብ ላይ ደግሞ ህዝቡን መተንኳከስ ጀምረዋል። ይህ ህዝባዊ አመፁ በቶሎ በቀጣይ ወደየት ሊዛመት እንደሚችል ሁሉ አውቀዋል አሳስቧቸዋል ማለት ነው።

የተገደሉት ብዙዎች ናቸው። እነዚህ ዜጎች ቤተሰብ ዘመድ ወዳጆች አላቸው። ሊናገሩላቸው አልደፈሩም። ወይ ሜዲያዎቻችን በቂ ጥረት አላደረጉም። ድምፃቸው በበቂ አይሰማም። በግፍ የተገደሉ ቤተሰቦች እመኑኝ ከናንተ በላይ ቢናገር የሚሰማ ድምፅ ያለው የለም። ቁጣችሁን

ምሬታችሁን ፍትህን ጮክ አድርጋችሁ እባካችሁ ተናገሩ ጠይቁ። አገር ውስጥ ያላችሁ ድምፃቸው ሊሰማ የሚችልበትን መንገድ የምታውቁ እርዱ። እስከተናገራችሁ አብራችሁ የሚቆምና የሚጮህ ሁሌም ይኖራል። ይህ ፈትህን ለማግኘትም ሆነ ይህ መራራ ሀዘን በሌሎች እንዳይደርስ በመከላከሉ ረገድ ዋና ነው።

የንፁህን ዜጎችን ፍጅት አምርረው የተፀየፉ ቢቸግራቸው ከዚህ በሗላ የሚመጣ መንግስት እዛ ቤተመንግሰት ውስጥ ቢሮውን ማድረግ የለበትም ብለው ፅፈው በተደጋጋሚ አንብቤያለው። የኛ መከራ ብዙ ነው። ዛሬም ሆነ ወደፊት ልጆች እነዚህ ብንፁህን ደም የጨቀዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቁጭ ብለው የሚማሩት እንዴት ነው?። ተምረውስ ቢወጡ ምን አይነት ዜጋ ነው የሚሆኑት። መንግስት የተሻለ ያስፈራራል ብሎ በቦንብ ጭምር ተማሪቤት ውስጥ እየጣለ ልጆችን እየፈጀ እንደሆነም ሁሉ ይታወቃል። ቤተሰብ ደግሞ ዝም ብሎ ልጆቹን ወደግድያ ቦታ ይልካል። ነገ ባለተራው ልጅ የማን እንደሆነ የሚያውቅ ይመስል። አስተማሪም ያልሞቱትንና ወደማጎርያ ያልተላኩትን ልጆች ሰብስቦ ማስተማሩን ቀጥለዋል።

ለለውጥ የቆሙ ሀይሎች እንዲተባበሩ ጊዜው ግድ ብሏል። ህዝብም ግፊት እያደረገ ነው። ተቃዋሚዎች አሁንም የሚያሳኩት ግን አይመስለኝም። ያልተሰራ የቤት ስራ መሆኑ ላይ ግን ማንም ሀላፊነት የወሰደ የለም። ማንን ብለው ሀላፊነት ይወስዳሉ። ለማንኛውም ህብረት ሲባል ወያኔ ካልሆነው ያብዛኛውን ዜጋ አመኔታ የሚያገኝ። ካገዛዙ ጋር ካሉትም ብዙዎችን ለለውጥ ከቆመው ወገን ጋር የሚያሰልፍ። አገሬውን ሁሉ በቀጥታ ትግሉ ላይ ተሳታፊ በማድረግ ትግላችንን ቀላልና በቶሎ አሸናፊ የሚያደርግ። ያሉ የመብት ጥያቄዎችን፤ ፍላጎቶችን፤ ስጋቶችን፤ ጥርጣሬዎችን፤ ፍራቻዎችን መመለስና ማስተናገድ የሚቻለው ነው። ባጠቃላይ ሰፊ ትብብርን ነው። ይህን በማድረግ <u>በደህና</u> ያንድ አገር ህዝቦች እንደሆንን ሊያሻግረን የሚቻለው ነው። ችግራችን የተባበረ አለመኖሩ አይደለም ። ተባበርን ያሉ ቡዙ አሉን። አባባሉን ልዋስና ከወያኔ ያነሰ ጥብቆ እየሆነ መፍትሄም አሸናፊም አመኔታም ማግኘት አለመቻላቸው ነው። የሚያሳኩት አይመስልም ያልኩት ከፊት ለፊት እየቀደሙ ታኮ የሚያስገቡ እያየው ስለሆነ ነው። ይህን አይነቱ ትብብር በዋናነት ግድ ያለው ትግሉን አስተባብሮና አቀናጅቶ ጉልበታምና አሸናፊ ለማድረግ

መሆኑ እየታወቀ የሰለቸና ፍይዳ የሌለው ስላማዊ ወይስ በመሳርያ የሚል ጭቅጭቅ ውስጥ ሊከቱት ይጥራሉ። በተመሳሳይ ለሽግግር ጊዜው እንጂ የበዙት አሉ የምንላቸው ልዩነቶች ነፃ በሆነ ምርጫና የህዝብ ተሳትፎ በሂደት ይግባኝ የሌለው ብይን እያገኙ እንደሚሄድ እየታወቀ። ትክክለኛው የሆነው መፍትሄ መስርያ ምንገድ ይህው በሆነበት ቁጭ ብላችሁ ተነጋገሩበት የሚባሉትን ቁም ነገሮች ትብብሩ ውስጥ የሚገቡ የማይገቡ ለመለያ እየተጠቀሙበት ነው። ትብብር ያሻው በደህና ተሻግረን በአንድ አገር ዜግነት ያሉ ልዩነቶች ላይ የዜጎችን ብይን በነፃ ምርጫ ለማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸትና መሸጋገርያ መስራት እንዲቻል ነው። እሰጥ አገባዎች መንግስታዊ፤ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ ማእቀፍ ውስጥ የሚካሄዱበትን የሚስተናገዱበትን መፍትሄ የሚፈለግባቸውን መንገድ ለማምጣት ነው አለቀ። በተረፈ የዚህች አገር ዜጎች አማራና ኦሮሞዎች ብቻ ይመስል አጠቃላይ አገራዊ ፖለቲካውንም ሆነ መፍትሄውንና ትብብሩን እነሱ ዙሪያ ማሽከርከሩ በጭራሽ አልተመቸኝም። አይሳካም ካሰኙኝ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው።

እንደሚያስቡት ትብሩን በባዶ ወረቀት ላይ አንድ ተብሎ ለመስራት ከሞከሩ አሁንም አይሳካም። እንደውም አደጋም አለው። ለምን ለሚለው መፀሀፍ መፃፍ ይቻላል። ለኔ የሚታየኝ ቀላል የሆነ አቋራጭ ግን አለ። አሁን ያለውን ህገመንግስትም ሆነ ፌደራሊዝምን መቀበል ነው። ማንም የማይክደው ሁለት ትላልቅ ጉድለቶች አሉት። አንድ አብሮነታችንና ኢትዮጵያዊነትን ላይ አውዳሚነት አለበት። ሁለት ፌደራሊዝሙ የውሸት ከዛም በላይ ቀፎ ነው። እነዚህ ሁለት ነገሮች ላይ ማስተካከያ መስራት። ዲሞክራሲ፤ ነፃ ምርጫ፤ የህግ የበላይነት፤ የሰባዊ መብት ከጨመርንበት ትክክለኛ መንገድ ላይ ነው ያለነው። በቀላሉ የበዛውን ዜጋ አመኔታ የሚያገኝ ሽግግር ሰራን ማለት ነው። ከላይ እንዳልኩት ነገ ከነገ ወዲያ ይህም ሆነ ሌሎች ቁም ነገሮች

አማራጭ ባለበትና በሰከነ መንገድ ቀስ ባለ በሂደት በኛ በዜጎች ብይን እየተስተካከለ ይሄዳል። ይህን መንገድ ምርጫ እንደማያደርጉት አውቃለው።ም እየተሰማም ነው።

የኛ ነገር ትግሉን ከፊት ሆነህ ባግባቡ ወደፊት ማስኬድ ሲያቅትህ በተራህ ከኋላ ትሆንና በተቃራኒ አቅጣጫ መሰብ ትጅምራለህ። ይህን ደግመን ደጋግመን ስላየነው እናውቀዋለን። አሁን የተፋፋመውን የዜጎች መራር መሰዋትነት ያለበት ህዝባዊ እንቢታ አገር አቀፋዊ መልክ ያልያዘው ስላልተሰራ እንደሆነ ህዝብም ድርጅቶቹም ያውቁታል። ሂደቱም አጋላጭ ነው። ምንም አይነት ማስፈራርያ በመሳል የተሻለ አሳቢና ተቆርቋሪ በመሆን ይህን እውነት ለመሸፈን መሞከሩ የትም አያደርስም። በቃ አልተሰራም።

ህዝባዊ እንቢታው ሊሰራበት አይደለም ባለቤት የለውም ብዬ እንቅጩን አጋልጨ ነበር። አለው ሲባል ከተባለ ብዬ ተውኩት። ለዚህ የተወሰኑት የትግሉን ሌላ ዘርፍ ሊሰራ ግድ የሚለውን አስቸጋሪ የሆነውን መሰዋትነት ባለበት ሙሉ ትኩረት ሰጥተው ሲሰሩ ነበር። ስህተተኛ የሚሆኑት ቢያስጠላኝም እዚህ ላይ ሌሎች ምንም እየሰሩበት እንዳልሆነ እያወቁ መለስተኛ ትኩረትና ስራ መስራት ሲቻል ባለ መሰራቱ ነው። ይህን ለማድረግ ሁለንተናዊ ድርጅታዊ አቅሙ ደግሞ አለ። በድርጅት ታቅፎ በአመት አንዴ ወይ ሁለቴ ድግስ እየደገሰ ዝም ብሎ ቦዝኖ የተቀመጠውን አበል ማሰራት ይቻል ነበር። ሌሎች ድርጅት እንጂ ስራ እሰከጭራሹ አይዳዳቸውም። ባለቤት የለውም ባልኩ ጊዜ ለምን አልባት ብዬ ህዝባዊ እንቢታው ክፍት ስራ ነው። ባለቤት ሁኑት ብዬ ነበር።

ጭቆና አስቀያሚና የፈጠጠ አድሎ ባለበት እንቢኝ ማለት ከፍረሀት ጋር ተዛምዶ የለውም። የግለሰብ እንጂ የህዝብ ፈሪ የለም። የቱኒዝያና የግብፅ ህዝብ ከአርባ አመት በኋላ አንድ ቀን ሲነሳ ደፋር አልሆነም!። የኦሮሞ ህዘብም እንዲሁ። በተመሳሳይ ነገን ካለማወቅ ጋርም አይዛመድም። ነገ ምንም ያህል ጨላማ መስሎ ይታየው ዛሬን በጭቆና በአድሎና በሰቆቃ ውስጥ መኖርን ምርጫው የሚያደርግ ህዝብ የለም። ያ ቢሆን ኖሮ የግብፅም ሆነ የኦሮሞ ህዘብም እንቢኝ አይሉም ነበር።

እየተጋባ ተጎራብቶ እሳት አየተዋዋሰ የሚኖር ህዝብ ማና ማንን ነው የሚፈራውስ የሚጠራጠረውስ። ጉድለትን ለመሸፈን ተብሎ ብቻ የአዲስ አባባን ህዘብ ቦዬ አደረጋችሁት። ገበሬ ወገኑ ከመሬቱ ተፈናቅሎ እስከልጆቹ በችጋር እንዲያልቅ እየተደረገ ነገ እዛ መሬት ላይ ለኔ ቤት ይሰራልኛል ብሎ ነው ያልተቀላቀለው ስድብ ነው። ተጠራጥሮ ፈርቶ እያላችሁ ህዝብ ላይ አታላኩ። ዜጋው እንቢኝ ለማለት እያሰበና እየፈለገ ትግሉን እንዴት ያስተባብርው እንዴት እንደሚጀምረው ነው ግራ የገባው። አለቀ። እየታገልኩ ነው ካለ አንድ ድርጅት ሊሰራለት ይገባ የነበረው ይህንኑ ነው። ጉድለቱን ሊሞሉ ይችሉ የነበሩ ሜዲያዎች፣ ፀሃፊዎችና ምሁራን ህዘብ ሊያደርግ የሚችለውን "እንዴት" መቼ" "በምን መንገድ" "በምን አይነት ጥንቃቄ" ብቻ ህዘብ ያለውን አቅምና ብዙ አማራጮች "ሀ" "ሁ" ብሎ ዝርዝር አድረጎ ከማስተማርና ህዘብን ከማዘጋጀት ይልቅ ችግሩን ብቻ ነጋ ጠባ በመንገር ተስፋ በማስቆረጥ ጉልበተኛነት እንዳይሰማው ነው የተደረገው። ከተመስገን ደስ ያለኝ ውጪ በቀጥታ ትግሉ ላይ የፃፉም በዚህ መንገድ የሞከረ አልነበረም። እሱንም ክፉ አካሄድ እንደሆነ ስላወቁ በቶሎ አስረው ዝም አሰኙት። የማሸነፍ ሚስጥሩ ተራ ከሚመስለው የፊት ገፁ አጠቃቀም ጀምሮ ከተመችቶኛል በማካፈል መረጃን ማዳረስ የትግሉ አካል እንደሆነ። ብቻ ህዝብ ያውቃል ተብሎ የሚተው፣ ቀላል የሆኑ፣ ሁላችን ልናደርጋቸው የሚቻሉን ነግሮችን ማስተማር እነደሆነ ግልፅ እያለ እየመጣ ነው።

ዳዊት ዳባ

Ethiomedia.com – February 6, 2016